እምነት እንደ ጋሻ አንሡ ። 17እንዲሁም ደኅን
ነትን እንደ ራስ ቊር በራሳችሁ ላይ ድፉ ፤ የእ
ግዚአብሔርን ቃል እንደ መንፈስ ቅዱስ ሰይፍ
ያዙ ። 18የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ስትለምኑ
በመንፈስ ቅዱስ እየተመራችሁ ዘወትር ጸልዩ ፤
በዚህ ዐይነት ንቅታችሁ ትጉ ፤ ለምእመናንም
ሁሉ ባለማቋረጥ ጸልዩ ፤ 19የወንጌልን ምስጢር
ያለ ፍርሃት እንድገልጥ ፥ በምናገርበት ጊዜ አስ
ፈላጊውን ቃል እንዲሰጠኝ ለእኔም ጸልዩልኝ ።
20አሁን እንኳ ታስሬ ሳለሁ የዚህ ወንጌል አም
ባሳደር ነኝ ፤ ስለዚህ እንደሚገባኝ ያለ ፍርሃት
እንድናገር ጸልዩልኝ ።

### የመጨረሻ ሰላምታ

21የተወደደው ወንድማችንና በጌታ ኢየሱስ
ሥራ ታማኝ አገልጋይ የሆነው ቲኪቆስ የእኔን
ሁኔታ እንድታውቁ ስለ እኔ ሁሉን ነገር ይነግ
ራችኋል ። 22ስለዚህ እኛ እንዴት እንደሆንን
እንድታውቁና እንዲያበረታታችሁም በማለት
እርሱን ወደ እናንተ ልኬዋለሁ ።
23ከእግዚአብሔር አብና ከጌታም ከኢየሱስ
ክርስቶስ ሰላምና ፍቅር ከእምነት ጋር ለወንድ
ሞች ይሁን ። 24በማያቋርጥ ፍቅር ጌታችንን ኢየ
ሱስ ክርስቶስን ከሚወዱ ሁሉ ጋር ጸጋ ይሁን ።

# የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
# ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

## መግቢያ

ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች የጻፈው መልእክት የተጻፈው መቄዶንያ በሚባለው የሮም ግዛት በምትገኘው በፊልጵስዩስ ላለችው ቤተ ክርስቲያን ነው ፤ ይህች ቤተ ክርስቲያን ጳውሎስ በአውሮፓ ምድር በመጀመሪያ ያቋቋማት ናት ፤ መልእክቱ የተጻፈው ጳውሎስ ከሌሎች ክርስቲያን አገልጋዮች ተቃውሞ በደረሰበትና በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን በተነሣው ሐሰተኛ ትምህርት ምክንያት ልቡ በሐዘን በተሰበረበት ጊዜ በእስር ቤት በሚገኝበት ወቅት ነው ፤ ይሁን እንጂ ጳውሎስ በኢየሱስ ክርስቶስ ያለው እምነት እጅግ የጠለቀ በመሆኑ በዚህ መልእክት ጐልቶ የሚታየው ደስታና ሙሉ መተማመን ነው ።

ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈበት ተቀዳሚ ምክንያት በችግሩ ጊዜ እርሱን ለመርዳት ስጦታ ልከውለት ስለነበር የፊልጵስዩስን ምእመናን ለማመስገን ነው ፤ ምንም እንኳ በእርሱም ሆነ በእነርሱ ላይ ልዩ ልዩ ችግር የደረሰ ቢሆንም ድፍረትና ሙሉ መተማመን እንዲኖራቸው በዚህ አጋጣሚ ያበረታታቸዋል ። ትዕቢትንና ትምክሕትን አስወግደው በኢየሱስ ክርስቶስ ትሕትና እንዲሞሉ በጥብቅ ያሳስባቸዋል ፤ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በመተባበር ያገኙት ሕይወት ከእግዚአብሔር ጸጋ ስጦታ የመነጨና በእምነት የተቀበሉት ነው እንጂ የአይሁዳውያንን ሥርዓቶች በመፈጸም የተገኘ አይደለም በማለት ያስታውሳቸዋል ፤ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በመተባበር ለሚኖሩ ሁሉ እግዚአብሔር ስለሚሰጣቸው ሰላምና ደስታም ይጽፍላቸዋል ።

ይህ መልእክት የሚታወቀው ደስታን ፥ መተማመንን ፥ ኅብረትንና በክርስትና እምነትና ሕይወት መጽናትን አጕልቶ በማሳየቱ ነው ፤ በተጨማሪም ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ያለውን ታላቅ ፍቅር ይገልጣል ።

6፥17 ፦ ኢሳ. 59፥17 ። 6፥21 ፦ ሐ.ሥ. 20፥4 ፤ 2ጢሞ. 4፥12 ። 6፥21-22 ፦ ቈላ. 4፥7-8 ።



## ምዕራፍ 1
### ሰላምታ

1ይህ መልእክት የኢየሱስ ክርስቶስ አገል.ጋ
ዮች ከሆኑት ከጳውሎስና ከጢሞቴዎስ የተላከ
ነው ፤
የተላከውም በፊልጵስዩስ ከተማ ለሚኖሩ ፥
በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናቸው ተቀድሰው ክር
ስቲያኖች ለሆኑ ሁሉ ፥ እንዲሁም ለቤተ ክርስ
ቲያን መሪዎችና ዲያቆናት ነው ።
2ከአባታችን ከእግዚአብሔር ፥ እንዲሁም
ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ
ይሁን ።

### የጳውሎስ የምስጋና ጸሎት

3እናንተን በማስታውስበት ጊዜ ሁሉ አምላ
ኬን አመሰግናለሁ ፤ 4ስለ ሁላችሁም በምጸልይ
በት ጊዜ ጸሎቴ በደስታ የተሞላ ነው ። 5ከመጀ
መሪያው ቀን አንሥቶ እስከ አሁን የምሥራቹን
ቃል በማወጅ የሥራዬ ተባባሪዎች ስለ ሆናችሁ
እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ፤ 6ይህን መል
ካም ሥራ በእናንተ ሕይወት ውስጥ የጀመረ
አምላክ ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ለፍርድ በሚመለስ
በት ቀን ወደ ፍጻሜ እንደሚያደርሰው እርግ
ጠኛ ነኝ ። 7እኔ ስለ ሁላችሁም እንደዚህ
ማሰብ ይገባኛል ፤ ምክንያቱም በሙሉ ልብ ስለ
ምወዳችሁ ነው ፤ ስለ እናንተ እንደዚህ የማስብ
በት ሌላው ምክንያት ደግሞ የምሥራቹን ቃል
መሠረት ለማስያዝ መከላከያዬን በማቀርብበት
ጊዜና አሁንም በእስራት ላይ ሳለሁ ፥ እናንተ
ከእኔ ጋር የእግዚአብሔር ጸጋ ተካፋዮች ስለሆ
ናችሁ ነው ። 8ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚወዳ
ችሁ ፥ እኔም የምወዳችሁ በመሆኔ ፥ በጣም እን
ደምናፍቃችሁ ምስክሬ እግዚአብሔር ነው ።
9ፍቅራችሁ ዕውቀትና ማስተዋል የሞላበት
ሆኖ እያደገ እንዲሄድ እጸልያለሁ ። 10ይኸ
ውም የተሻለውን ነገር መርምራችሁ እንድታ
ውቁና ክርስቶስ ተመልሶ በሚመጣበት ቀን
ንጹሖችና ነውር የሌለባችሁ ሆናችሁ እንድት
ገኙ ነው ። 11በዚህም ዐይነት ሕይወታችሁ ፥
ኢየሱስ ክርስቶስ በሚሰጣችሁ የጽድቅ ፍሬ
የተሞላ ሆኖ ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና
የምታስገኙ ትሆናላችሁ ።

### የጳውሎስ መታሰር የምሥራቹ ቃል እንዳይስፋፋ አላደረገም

12ወንድሞቼ ሆይ! በእኔ ላይ የደረሰው
ነገር ሁሉ የምሥራቹ ቃል በይበልጥ እንዲስ
ፋፋ ማድረጉን እንድታውቁ እወዳለሁ ።
13እኔም የታሰርሁት በክርስቶስ የምሥራች
ቃል ምክንያት መሆኑን የቤተ መንግሥት ዘበ
ኞችና ሌሎችም እዚያ ያሉት ሰዎች ሁሉ ያው
ቃሉ ። 14በእኔ መታሰር ምክንያት ከአማኞች
ወንድሞች ብዙዎቹ በይበልጥ በጌታ የሚተማ
መኑ ሆነዋል ፤ ስለዚህ የምሥራቹን ቃል[1*] ያለ
ፍርሃት ለማብሠር ከቀድሞ የበለጠ ድፍረት
አግኝተዋል ።
15ይሁን እንጂ አንዳንዶቹ የክርስቶስን የም
ሥራች ቃል የሚያበሥሩት በቅንአትና በጥላቻ
መንፈስ ነው ፤ ሌሎቹ ግን የክርስቶስን የምሥ
ራች ቃል የሚያበሥሩት በቅን ልቦና ነው ።
16እነዚህ የምሥራቹን ቃል በቅን ልቦና የሚያ
በሥሩት ከፍቅር የተነሣ ነው ፤ እነርሱም ይህን
የሚያደርጉት እኔ የክርስቶስን የምሥራች ቃል
ለማብሠር የተሾምሁ መሆኔን ስለሚያውቁ
ነው ። 17እነዚያ ግን የምሥራቹን ቃል አጣም
መው የሚሰብኩት ራሳቸውን ከፍ ከፍ ለማድ
ረግ ካላቸው ምኞት የተነሣ ፥ በእስራቴ ተጨ
ማሪ ችግር ሊያመጡብኝ አስበው ነው ።
18ያም ሆነ ይህ በዚህ ሁሉ ደስ ይለኛል ፤
ወደ ፊትም ለደስታዬ ወሰን አይኖረውም ፤ ምክ
ንያቱም በመልካምም ሆነ በክፉ አስተሳሰብ
በሁሉም መንገድ የክርስቶስ የምሥራች ቃል
ይነገራል ። 19ሌላው የምደሰትበት ምክንያት
በእናንተ ጸሎትና በኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ
ዕርዳታ ነፃ እንደምወጣ ስለማውቅ ነው ።
20ስለሆነም በምንም ነገር እንደማልሸነፍ
ፍጹም መተማመንና ሙሉ ተስፋ አለኝ ፤ እን
ዲሁም ከምንጊዜውም ይልቅ አሁን በሕይወት
ብኖርም ወይም ብሞት በሁለንተናዬ ክርስቶስ
እንዲከብር ለማድረግ ሙሉ ድፍረት አለኝ ።
21ስለዚህ ለእኔ ሕይወት ማለት ፥ በክርስቶስ
መኖር ነው ፤ ሞትም ማለት ፥ ጥቅም የሚገኝ
በት ነገር ነው ። 22ይሁን እንጂ በሕይወት
መኖሬ የሥራ ፍሬ የሚሰጥ ከሆነ ፥ ከሕይወትና
ከሞት የትኛውን እንደምመርጥ አላውቅም ።
23በእነዚህ በሁለቱ አሳቦች መካከል ተይዣ
ለሁ ፤ በአንድ በኩል ከዚህ ሕይወት ተለይቼ
ከክርስቶስ ጋር መሆን እፈልጋለሁ ፤ ምክንያ
ቱም ከክርስቶስ ጋር መሆን ከሁሉ የሚበልጥ
ነገር ስለሆነ ነው ። 24በሌላ በኩል እናንተን
ለመጥቀም በሕይወት መኖሬ በጣም አስፈላጊ
እንደሆነ አስባለሁ ። 25በዚህም አቅጣጫ ያለው
አሳቤ ስለሚያመዝን ከሞት አምልጬ ከእናንተ
ከሁላችሁም ጋር እንደምኖር እርግጠኛ ነኝ ፤
ይህም ከሆነ በእምነት ዕድገትና ደስታን ታገኛ
ላችሁ ። 26እኔም እንደገና ከእናንተ ጋር ስገኝ
በእኔ ምክንያት በኢየሱስ ክርስቶስ ያላችሁ
ትምክሕት ይበዛል ።

1* 1፥14 የምሥራቹን ቃል ፦ አንዳንድ ቅጂዎች "የእግዚአብሔርን ቃል" ይላሉ ።
1፥1 ፦ ሐ.ሥ. 16፥12 ። 1፥13 ፦ ሐ.ሥ. 28፥30 ።

27 እንግዲህ በጣም አስፈላጊው ነገር ሕይወ
ታችሁ የክርስቶስን የምሥራች ቃል የሚያስመ
ሰግን እንዲሆን ነው ፤ ይህም ከሆነ መጥቼ ባያ
ችሁም ወይም ከእናንተ ብርቅም በአንድ ዓላማ
ጸንታችሁ መቆማችሁንና የምሥራቹን ቃል በኅ
ብረት ለማዳረስ መጋደላችሁን እሰማለሁ ።
28 ተቃዋሚዎቻችሁንም በምንም ነገር አትፍሩ
አቸው ፤ ይህም ድፍረታችሁ ለእነርሱ የመሸ
ነፍ ምልክት ሲሆን ፣ ለእናንተ ግን በእግዚአብ
ሔር ኀይል የማሸነፍ ምልክታችሁ ነው ።
29 ክርስቶስን የማገልገል ዕድል የተሰጣችሁም ፣
በእርሱ በማመናችሁ ብቻ ሳይሆን ፣ በእርሱ
ምክንያት መከራ በመቀበላችሁ ጭምር ነው ።
30 ስለዚህ አሁን ከእኔ ጋር የመከራ ተካፋዮች
ሆናችኋል ፤ ይህም መከራ ከዚህ በፊት እንደደረ
ሰብኝ የምታውቁትና አሁንም በመከራ ውስጥ
መሆኔን የምትሰሙት ነው ።

## ምዕራፍ 2
### የክርስቶስ ትሕትና ምሳሌነት

1 የክርስቶስ እንደመሆናችሁ መጠን ፣ እርስ
በርስ በመመካከር በርትታችኋል ፤ በክርስቶስ
ፍቅር ተጽናንታችኋል ፤ በመንፈስ ቅዱስ አንድ
ነትን አግኝታችኋል ፤ እርስ በርሳችሁ ደግነት
ንና ርኅራኄን አሳይታችኋል ፤ 2 ስለዚህ በአ
ሳብ ፣ በፍቅር ፣ በመንፈስ ፣ በዓላማ እየተስማማ
ችሁ ደስታዬ ሙሉ እንዲሆን አድርጉ ። 3 በት
ሕትና ተሞልታችሁ ሌሎች ሰዎች ከእናንተ
እንደሚሻሉ አድርጋችሁ ቍጠሩ እንጂ ወገን
በመለየትና በራስ ወዳድነት ወይም “ያለ እኔ
ማን አለ” በሚል ትምክሕት ምንም ነገር አታ
ድርጉ ። 4 እንዲሁም እያንዳንዱ የራሱን ጥቅም
ብቻ ሳይሆን የሌላውንም ሰው ጥቅም ያስብ ።
5 በዚህ ዐይነት ኢየሱስ ክርስቶስ ያሳየው የትሕ
ትና ጠባይ በእናንተም ሕይወት ሊኖር ይገ
ባል ።

6 እርሱ የመለኮት ባሕርይ አለው ፤
ይሁን እንጂ ፣ ከእግዚአብሔር ጋር
እኩል የሚያደርገውን
የመለኮት ባሕርይ እንደያዘ መቅረት
አልፈለገም ።
7 ይልቁንም ያለውን ክብር በገዛ ፈቃዱ
ትቶ ፣
አገልጋይ መሆንን መረጠ ፤
በሰው ምሳሌም ተገለጠ ።
8 እንደ ሰው ሆኖም በትሕትና ራሱን ዝቅ
አደረገ ፤
እስከ ሞት ድረስ ፣
ያውም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እስከ
መሞት ድረስ
ታዛዥ ሆነ ።
9 በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ከሁሉ
በላይ ወዳለው
የክብር ስፍራ ከፍ አደረገው ፤
ከስም ሁሉ የሚበልጠውንም ስም
ሰጠው ።
10 ስለዚህ ለኢየሱስ ስም ክብር
በሰማይና በምድር ፣ ከምድር በታች
ያሉት ሁሉ
በጕልበታቸው ይንበረከካሉ ።
11 በምላሳቸውም
“ኢየሱስ ክርስቶስ በእርግጥ ጌታ
ነው” ብለው በመመስከር ፣
ለእግዚአብሔር አብ ክብር ይሰጣሉ ።

### ለዓለም ሰዎች ብርሃን ስለመሆን

12 ወዳጆቼ ሆይ! እኔ ከእናንተ ጋር በነበርሁ
በት ጊዜ ዘወትር ታዛዦች ነበራችሁ ፤ ይልቁ
ንም አሁን ከእናንተ በራቅሁበት ጊዜ ይበልጥ
ታዛዦች እንድትሆኑ አሳስባችኋለሁ ፤ ስለዚህ
እያንዳንዳችሁ ያላችሁን ደኅንነት ፍጹም ለማ
ድረግ በፍርሃትና በአክብሮት ተግታችሁ ሥሩ ።
13 ምክንያቱም እግዚአብሔር ፈቃደኛነትንና
ታዛዥነትን ለእናንተ እየሰጠ ዓላማውን ከፍጻሜ
ለማድረስ በእናንተ ውስጥ ይሠራል ።
14 ማናቸውንም ሥራ በምትሠሩበት ጊዜ
አታጕረምርሙ ወይም በቊጣ አትከራከሩ ።
15 ይህም ከሆነ በዚህ በጠማማና በሥርዓት አል
በኛ ትውልድ መካከል ፣ ነውርና ነቀፋ የሌለባ
ችሁ ንጹሐን የእግዚአብሔር ልጆች በመሆን ፣
ለዓለም ሕዝብ እንደ ከዋክብት ታበራላችሁ ።
16 ይህም የሚሆነው ሕይወት የሚገኝበትን የም
ሥራች ቃል ባለማቋረጥ ማብሠር ስትችሉ ነው ፤
በዚህ ዐይነት ሩጫዬም ሆነ ሥራዬ ከንቱ ሆኖ ስለ
ማይቀር ፣ ክርስቶስ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ
የምመካበት ምክንያት ይኖረኛል ማለት ነው ።
17 ለእግዚአብሔር በእምነት በምታቀርቡት
መሥዋዕትና አገልግሎት ላይ የእኔም ሕይወት
ተጨማሪ መሥዋዕት ሆኖ ቢቀርብ እንኳ ደስ
ይለኛል ፤ እናንተም የደስታዬ ተካፋዮች ትሆና
ላችሁ ። 18 እንዲሁም እናንተ ተደስታችሁ ፣
እኔንም የደስታችሁ ተካፋይ ታደርጉኛላችሁ ።

### የጢሞቴዎስና የኤፓፍሮዲቱስ አገልግሎት

19 እኔ ስለ እናንተ ሁኔታ በመስማት እንድጽ
ናና ጢሞቴዎስን በፍጥነት ወደ እናንተ ለመ
ላክ እንደሚያስችለኝ በጌታ ኢየሱስ ተስፋ አደ
ርጋለሁ ። 20 ስለ እናንተ ሁኔታ እንደ እኔ እየተ
ጨነቀ የሚያስብ ከጢሞቴዎስ በቀር ሌላ ሰው
የለኝም ። 21 ሌሎቹ ግን የራሳቸውን ጥቅም
ብቻ ያሳድዳሉ እንጂ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ





ሥራ ግድ የላቸውም ። 22 ጢሞቴዎስ ፣ ታማኝ
ነቱ ተፈትኖ የተረጋገጠለት ጠቃሚ ሰው መሆ
ኑንና ከእኔም ጋር እንደ አባትና ልጅ ተባብረን
የምሥራቹን ቃል በማብሠር አብረን ስንሠራ
መቆየታችንን እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁ ።
23 ስለዚህ የእኔ ጉዳይ ከምን እንደሚደርስ ከተ
ረዳሁ በኋላ ፣ ጢሞቴዎስን በፍጥነት ወደ እና
ንተ እንደምልክላችሁ ተስፋ አደርጋለሁ ።
24 እንዲያውም እኔ ራሴ ወደ እናንተ መምጣት
እንድችል ጌታ ይረዳኛል ብዬ እተማመናለሁ ።
25 እንዲሁም እኔን እንዲረዳኝ ልካችሁት የነ
በረውን ፣ በጌታ ወንድማችን የሆነውን ፣ ኤፓፍ
ሮዲቱስን ወደ እናንተ መላክ አስፈላጊ ሆኖ አግ
ኝቼዋለሁ ፤ እርሱ ከእኔ ጋር የኢየሱስ ክርስቶስ
ወታደር በመሆን በትጋት አብሮኝ ሲሠራ የቆየ
ነው ። 26 እርሱን ወደ እናንተ የምልከውም ሁላ
ችሁንም ለማየት በመናፈቁና መታመሙንም ስለ
ሰማችሁ በሐዘን ስሜት በመዋጡ ነው ። 27 በእር
ግጥ በጠና ታሞ ፣ ለሞት ተቃርቦ ነበር ፤ ነገር
ግን እግዚአብሔር ራራለት አድኖታል ። ለእር
ሱም ብቻ ሳይሆን ለእኔም ስለራራልኝ ሐዘን በሐ
ዘን ላይ እንዳይደራረብብኝ አድርጎአል ። 28 ስለ
ዚህ እናንተ እርሱን በማየት እንድትደሰቱና የእ
ኔም ሐዘን እንዲቃለል እርሱን ወደ እናንተ ልል
ከው በይበልጥ ፈለግሁ ። 29 እንግዲህ በጌታ ወን
ድማችሁ መሆኑን በመገንዘብ በደስታ ተቀበ
ሉት ፤ እንደ እርሱ ያሉትንም ሰዎች ሁሉ አክብ
ሩአቸው ። 30 ምክንያቱም እናንተ በቅርብ ተገኝ
ታችሁ ልታደርጉልኝ ያልቻላችሁትን ዕርዳታ
እርሱ ለማሟላት ብሎ የክርስቶስን የምሥራች
ቃል በማብሠር ተግባር ለሕይወቱ ሳይሳሳ ለሞት
ተቃርቦ ነበር ።

## ምዕራፍ 3
### እውነተኛ ጽድቅ

1 በተረፈ ወንድሞቼ ሆይ! የጌታ ደስታ ይብ
ዛላችሁ ፤ ያንን ከዚህ በፊት የጻፍሁላችሁን
ነገር ደግሜ ብጽፍላችሁ እኔን አያሰለቸኝም ፤
እናንተን ግን ከስሕተት ሊጠብቃችሁ ይችላል ።
2 እንደ ውሻ ከሚልከፈከፉ ከክፉዎች አስተማሪ
ዎች ተጠንቀቁ ፤ እነርሱ ስለ መገረዝ ሐሰተኛ
ትምህርት የሚያስተምሩ ናቸው ። 3 እኛ እግዚ
አብሔርን በመንፈስ የምናመልክና በውጫዊ
ሥርዓት ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ የምን
መካ ስለሆንን በእውነት ተገርዘናል ። 4 ትምክ
ሕት የሚያስፈልግ ከሆነ እኔ በብዙ ነገር
ልመካ እችላለሁ ፤ በውጫዊ ሥርዓት የሚመካ
ቢኖር ፣ እኔ ከእርሱ ይበልጥ የምመካበት ብዙ
ምክንያት አለኝ ። 5 እኔ በተወለድሁ በስምንተ
ኛው ቀን ተገርዤለሁ ፤ በትውልዴም ቢብንያም
ዘር የሆንሁ እስራኤላዊ ነኝ ፤ ከዚህም በቀር
ጥርት ያልሁ ዕብራዊ ነኝ ። የአይሁዳውያንን
ሕግ ስለመጠበቅም ቢሆን ፣ ፈሪሳዊ ነበርሁ ።
6 ስለ ሃይማኖት በመቅናትም ቢሆን ፣ በኢየሱስ
ክርስቶስ የሚያምኑትን የማሳድድ ነበርሁ ።
ሕግን በመጠበቅ ስለመጽደቅም ቢሆን ፣ ያለ
ነቀፋ እኖር ነበርሁ ። 7 እንግዲህ ከዚህ በፊት
ጠቃሚዎች ናቸው ብዬ አምንባቸው የነበሩትን
ነገሮች ሁሉ ስለ ክርስቶስ ብዬ ዋጋ እንደሌላ
ቸው ከንቱ ነገሮች አድርጌ እቈጥራቸዋለሁ ።
8 ከዚህም በቀር ጌታዬን ኢየሱስ ክርስቶስን ከማ
ወቅ የበለጠ ሌላ ምንም ነገር እንደሌለ ስለማ
ምን ሁሉን ነገር እንደ ኪሣራ እቈጥረዋለሁ ፤
ስለ እርሱም ሁሉን ነገር አጥቻለሁ ። ክርስቶስ
ንም ለማግኘት ስል ሁሉን ነገር እንደ ቤት
ጥራጊ እቈጥራለሁ ። 9 ይህንንም የማደርግበት
ምክንያት በሕግ ላይ የተመሠረተውን የራሴን
ጽድቅ ትቼ ፣ በእምነት ላይ የተመሠረተውን
የእግዚአብሔርን ጽድቅ በክርስቶስ አማካይነት
ለማግኘትና ከእርሱም ጋር ለመሆን ነው ።
10 ሌላው ምክንያት ክርስቶስንና የክርስቶስን
የትንሣኤ ኀይል ለማወቅ ፣ በሞቱም እርሱን
ለመምሰልና የመከራው ተካፋይ ለመሆን ነው ።
11 እንዲሁም ከሞትሁ በኋላ ተነሥቼ ለዘላለም
በሕይወት ለመኖር ተስፋ በማድረግ ነው ።

### ወደ ግብ ለመድረስ መሮጥ

12 ይህን ሁሉ ገና አላገኘሁም ፤ ወይም
በዚህ ሁሉ ፍጹም ሆኜአለሁ ለማለት አልች
ልም ፤ ይሁን እንጂ ኢየሱስ ክርስቶስ እኔን የእ
ርሱ አድርጎ ያዘጋጀልኝን ሽልማት ለማግኘት
ወደፊት በመሮጥ እተጋለሁ ። 13 ወንድሞቼ
ሆይ! ገና ወደዚያ እንደደረስሁ አልቈጥርም ፤
ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ ፤ ይኸውም
በስተኋላዬ የነበረውን እየረሳሁ ፣ በፊቴ ያለውን
ለመያዝ እተጋለሁ ። 14 ሽልማቴንም ለማግኘት
በፊቴ ወዳለው ግብ እሮጣለሁ ፤ ይህም ሽልማት
እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት
ወደ ላይ ጠርቶ የሚሰጠኝ ሕይወት ነው ።
15 እንግዲህ በመንፈሳዊ ሕይወት የጠነከርን
ሁሉ ይህን የመሰለ አስተሳሰብ ሊኖረን ይገባል ፤
የምትለያዩበት አሳብ በመካከላችሁ ቢኖር ፣ ይህ
ንንም አሳብ እግዚአብሔር ግልጥ ያደርግ
ላችኋል ። 16 ያም ሆነ ይህ ፣ አካሄዳችን አሁን
ከደረስንበት መንፈሳዊ ሕይወት ጋር ተመጣ
ጣኝ ይሁን ።
17 ወንድሞቼ ሆይ! የእኔን ምሳሌነት ለመከ
ተል ተባበሩ ፤ የእኛንም ምሳሌነት የሚከተሉ
ትን ሁሉ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ ። 18 ምክንያ
ቱም ከአሁን በፊት ብዙ ጊዜ እንደ ነገርሁአች
ሁና አሁንም በሐዘን እምባዬን እያፈሰስሁ እን
ደምነግራችሁ ሁሉ ፣ ብዙዎቹ በአካሄዳቸው

